d) አካል ወይም አካላት ማለት እያንዳንዱ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፣ ቡድን ወይም ጉዳዩ እንደሚመለከተው አካል የተሰየመ ወይም ተቀባይነት ያለው አካል፥ ተማሪን፣ ወላጅን፣ የወላጅ ምትክ ወይም የተማሪን አሳዳጊን እና ሱፐር ኢንተንደንትን ያካትታል። ችሎቱን የሚመራዉ ኦፊሰር አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ በተግባር በማሳየት ሌላ ማንኛውንም ሰው፣ ቡድን፣ ወይም አካል ለዉስን ዓላማዎች እንዲሳተፉ እንደሁኔታው ሊፈቅድ ይችላል።

e) ችሎቱን የሚመራው ኦፊሰር ማለት ጉዳዩ በችሎት ከመታየቱ በፊት ምርመራ የሚያካሄድ የችሎት መርማሪ ማለት ነው። ቦርዱ ለሚያካሄደው ችሎት መሪ/ሰብሳቢ ማለት ፕሬዚዳንቱ ነው፤ ወይም ፕሬዚዳንት በማይኖሩበት ጊዜ ምክትል ፕሬዝዳንት፤ ወይም ሁለቱም በሌሉበት ጊዜ፣ በፕሬዚዳንቱ/ቷ የተወከለ/ች አባል፣ ወይም እንደዚህ ዓይነት ስያሜ/ዉክልና በሌለበት ጊዜ በቦርዱ የሚሰየም ይሆናል።

f) ሱፐርኢንተንደንት ማለት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ ማለት ነዉ

g) የጽሁፍ ማስታወቂያ በዚህ ህግ መሰረት የተሟላ የሚሆነው—

(1) አቅራቢው ወገን በእጅ ከሰጠ ወይም በትክክል ሲያደርስ ነው፣

(2) ሠነዶቹን በዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ ቤት ተመዝግቦ ወይም በመልክት ማረጋገጫ ፖስታ ወይም ኤክስፐረስ ሜይል ማስገባት ወይም Fed Ex፣ UPS ወይም DHL በመሣሰሉ የፖስታ አገልግሎት ተቋም አማካይነት ተልኮ መልክቱን ከመነሻው ክትትል ማድረግና ማረጋገጥ የሚያስችል ሲሆን ወይም ሠነዶቹ በአድራሻ ከተላኩበት ቀን በፊት MCPS መዝገብ ላይ የሚታይ ከሆነ፣ ወይም

(3) በሌላዉ አካል በኢ-ሜይል የተላከ መሆኑን ለማረጋገጥ ከተጠየቀ ኢ- ሜይል የተላከበት ቀን የሚረጋገጥ ከሆነ ነው።

2. ተፈፃሚነት

a) ይህ ህግ በቦርዱ የዳኝነት /quasi-judicial ኃላፊነቶች ውስጥ ይግባኞችን እና ችሎቶችን የማከናወን መመሪያ ይሆናል። የቦርድን ህግ ለማውጣት ወይም ፖሊሲ የማውጣት ተግባሮችን በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆኑም።

b) በእነዚህ ደንቦች የተካተቱ ሂደቶች በትምህርት አንቀጽ፣ ንኡስ አንቀጽ 4-205(c)፣ 7-305፣ 6-202፣ እና 6-203 እና በአካባቢው የቦርድ አሠራር ሂደት በትምህርት አንቀፅ ውስጥ ተገልፀዋል።

(1) በአንቀጽ 4-205(c) የተመለከቱት አፈጻጸሞች የቦርዱ ህጎች እና መመሪያዎችን ወይም የካውንቲውን የህዝብ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ስርዓት በሚመለከቱ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች ላይ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በሚወስኑት ይግባኝ ላይ ነው። በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ እንደዚህ አይነት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔዎች በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ መቅረብ አለባቸው።

(2) በአንቀጽ 6-202(a) ስር ያሉ አጣሪ ችሎቶች የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

የምስክር ወረቀት ያላቸውን ሰራተኞች ለማገድ ወይም ለማባረር በሚያቀርቡት ሀሳብ ላይ ያተኮረ ነው። (ክፍል 6-201(b)(iv))።

(3) በአንቀጽ 6-203 ስር ያሉት ችሎቶች ለመጀመሪያ ችሎት በቦርዱ የሚመሩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸዉ።

(4) በአንቀጽ 7-305(c) ስር የይግባኝ ማጣሪያ ችሎቶች ተማሪዎችን ከአስር የትምህርት ቀናት በላይ ማገድ ወይም ለማባረር የሚያስችል በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተረጋገጠ ሲሆን ነው። በሜሪላንድ ህግ፣ እንደዚህ አይነት እገዳዎች በ10 ቀናት ውስጥ ይግባኝ መቅረብ አለባቸው።

3. ስለ አጣሪ ችሎት ይግባኝ ወይም ጥያቄዎች/አቤቱታዎች-አንቀጽ 4 - 205 (c)

a) ለቦርድ የሚቀርቡት አቤቱታዎች በሙሉ ይግባኝ አቅራቢው/ዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ከት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተሰጠ የመጨረሻ እርምጃ ወይም ውሳኔ መሆን አለባቸው። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቀረበው ይግባኝ ላይ በ45 ቀናት ውስጥ እርምጃ ለመውሰድ አለመቻል፣ በይግባኝ አቀራረብ ሂደት፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለቦርዱ መቅረብ ያለበትን ይግባኝ ውድቅ እንደማድረግ ሊቆጠር ይችላል።

b) በአንቀጽ 4-205(c) መሠረት እያንዳንዱ ለቦርድ መቅረብ ያለበት ይግባኝ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ በወሰደው የመጨረሻ እርምጃ ወይም ውሳኔ ይግባኝ ባይን ይጎዳል ተብሎ ሚታሰብ ከሆነ በ30 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማስታወቂያ ለቦርዱ በማቅረብ መጀመር አለበት። እያንዳንዱ የይግባኝ አቤቱታ ይግባኙን በሚወስደው አካል መፈረም እና የእያንዳንዱን ወገን ስም የተጻፈበት፣ መደበኛ ደብዳቤ እና የኢሜል አድራሻ ሊኖረው ይገባል።

c) በይግባኝ ማስታወቂያ ወይም የይግባኝ ማስታወቂያ ከገባ በ10 ቀናት ውስጥ፣ ይግባኙን ያስገባው ግለሰብ ወይም ሰዎች ለቦርዱ፣ ቅጂውን ለት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት እንደሚከተለው ማቅረብ አለባቸው።

(1) በቦርዱ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለይግባኝ የቀረቡት ጉዳዮች ግልጽ/አጭር መግለጫ

(2) ይግባኝ ባይ(ዮች) ይግባኙን ይደግፋል ብለው ያመኑባቸውን ማስረጃዎች ግልጽ/አጭር መግለጫ

(3) በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ዘንድ በይግባኝ አቅራቢ(ዎች) ክርክር የተደረገባቸው የትኛውም እውነታዎች፣ ካሉ፣ የጽሑፍ መግለጫ

(4) አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ወይም በይግባኝ አቅራቢው (ዎች) እጅ ያሉ የሁሉም ሰነዶች ቅጂ

d) በአንቀጽ 3 c) አስፈላጊውን መረጃ እና ሰነድ ከተረከበ በኋላ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ የሚደግፍ ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነዶችን ማቅረብ እና ቅጂውን ይግባኙ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ያደርጋል/ታደርጋለች።

(a) የተካተቱት ጉዳዮች ህገ-መንግስታዊ ወይም ትርጉም ባለዉ መልኩ ለህዝብ አስፈላጊ መሆናቸዉን፣

(b) የተነሱት ጉዳዮች መፍትሄ በትምህርት ስርአቱ አስተዳደር ውስጥ ቀዳሚ እሴት ሊኖረው የሚችል መሆኑን፣

(c) የተነሳዉ ጉዳይ ወይም የተነሱት ጉዳዮች የአንድን በጣም አስፈላጊ ሰራተኛ መብት መወሰንን የሚጠይቁ ከሆነ እና አሁን ባለው የይግባኝ ሂደት አጥጋቢ በሆነ መልኩ ፍርድ ሊሰጥ የማይችል ከሆነ፣ እና/ወይም

(d) በቦርዱ በተወሰነው መሠረት አግባብነት ያላቸው ሌሎች ምክንያቶች።

k) ማስረጃ የሚደመጥባቸው ችሎቶች አስፈላጊነትን ቦርዱ በሚወስንባቸዉ ሁኔታዎች፣ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ጉዳዩን ወደ ችሎት መርማሪ ለመላክ/ለማስተላለፍ የሚወስነው ካልሆነ በስተቀር፣ ቦርዱ እንዲህ ዓይነቱን ችሎት ያካሂዳል። ቦርዱ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ወደ ችሎት መርማሪ መምራት እንዳለበት እና እንደሌለበት ለመወሰን በመጀመሪያ ደረጃ ግንዛቤ ዉስጥ ከሚያስገባቸዉ ጉዳዮች መካከል፦

(1) ረዘም ያለ ማስረጃ የሚደመጥበት ችሎት የሚጠይቅ በክርክሩ ዉስጥ እዉነታዎች ስለመኖራቸዉ፣ እና/ወይም

(2) ጉዳዩ ለቦርድ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በችሎት መርማሪ የሚገመገም ሰፋ ያለ ሪኮርድ፣ በርካታ ሰነዶች፣ ወይም ተጨማሪ መረጃ መኖሩን ቦርዱ ከተሰማዉ/ካሰበ።

4. የይግባኝ ጥያቄ ወይም የመርማሪ ችሎት ጥያቄዎች– አንቀጽ 6-202(a) and 7-305(c)

a) አንቀጽ 6-202(a)

(1) በአንቀጽ 6-202(a) ድንጋጌ መሠረት ለቦርዱ አጣሪ ችሎት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርበው ሀሳብ አስተማሪን፣ ርእሰ መምህርን፣ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንትን ወይም ሌላ ሠርተፊኬት ያለውን ሰራተኛ ከሥራ ለማገድ ወይም ማሰናበትን የሚመለከት ከሆነ ነው።

(2) አንቀጽ 6-202(a) ስር እንደተገለጸው (ሠርተፊኬት ያለውን ሰራተኛ ከሥራ እንዲታገድ ወይም ከሥራ እንዲባረር) የሚቀርብ አስተያየት ቦርዱ ጽሑፉን በግልባጭ ለግለሰቡ(ቧ) ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ አጣሪ ችሎት እንዲካሄድ ለቦርዱ በጽሁፍ ጥያቄ ይቀባል። ባለጉዳዩ የተጠየቀበትን ክስ ግልባጭ እና የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳብ እና ስለ ስብሰባው (ከጽሁፍ ማሳወቂያው ከ10 ቀናት በላይ ከሆነ) የይግባኝ ችሎት ካልተጠየቀ የውሳኔ ሃሳቡ በቦርዱ እንደሚጸድቅ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይሰጣል።

(a) በአንቀጽ 6-202 (a) ድንጋጌ መሰረት እንዲህ ዓይነቱ ማሳወቂያ ግለሰቡ(ቧ) ለቦርድ የይግባኝ ችሎት ጥያቄ የማቅረብ መብት ወይም፣ በአማራጭ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የመጠየቅ መብት እንዳለዉ/እንዳላት ጭምር

(2) በአንቀጽ 7-305(c) ስር ያሉ ሁሉም የክርክር ችሎት ጥያቄዎች (የተማሪ ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረር) ቦርዱ በራሱ ምርጫ ወይም የቦርዱ ኮሚቴ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ መመልከት እንዳለበት ካልተወሰነ በስተቀር ወደ መርማሪ ችሎት ይላካሉ። ቦርዱ በመጀመሪያ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ለማየት/ለመስማት ፍላጎት እንዳለዉ ሊወስን ከሚያስችለዉ ምክንያቶች መካከል፦

(a) ባለመግባባቱ ውስጥ ተጨባጭ እውነታዎች የማይታዩ ከሆነ ወይም ባልተራዘመ ጊዜ መረጃ የሚቀርብበት ችሎት ካልሆነ፣

(b) ለጉዳዩ አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት እጅግ አስፈላጊነት ካለው፣ እና/ወይም

(c) የጉዳዩ ለህዝብ አስፈላጊነት ካለው፣ ለትምህርት ስርዓቱ አስተዳደር አስፈላጊነት ካለው፣ ወይም በባህሪዉ አሳሳቢ ስጋት ኖሮት ቦርዱ ማስረጃውን መስማት እንዳለበት ድምዳሜ ላይ ሲደረስ።

(3) ወላጅ/ተማሪ/ህጋዊ አሳዳጊ በችሎት የመስማት መብትን ለመተው ከፈለገ(ች) (አንቀጽ 7-305(c)) ይህ መብት የሚመለከተው የተማሪን ከአስር የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረርን ብቻ ነው፤ (1) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሂደቶች በመከተል ጉዳዩ በጽሑፍ ሪከርድ እንዲወሰን መጠየቅ እና/ወይም (2) በቦርዱ ፊት የቃል ክርክር ብቻ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

(a) ጉዳዩ በጽሁፍ ሪከርድ እንዲታይ የጠየቀ(ች)ው ግለሰብ ወይም ሰዎች ግልባጭ ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በማድረግ ለቦርዱ የሚከተለውን ማቅረብ አለባቸው።

(i) በይግባኙ ላይ የቀረቡ ጉዳዮች አጭር መግለጫ

(ii) ይግባኝ ባይ(ዮች) ይግባኙን ይደግፋል ብለው ያመኑባቸው እውነታዎች አጭር መግለጫ

(iii) ይግባኝ አቅራቢው (ዎች) የማይስማሙበትና ክርክር የሚያደርጉት በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ከተገለጹት እውነታዎች በየትኛው ጭብጥ ላይ እንደማይስማሙበት የጽሑፍ መግለጫ ማቅረብ

(iv) ተዛማጅነት አላቸዉ ተብለው የሚታመኑ ወይም እምነት የሚጣልባቸዉ እና በይግባኝ ባይ(ዮች) እጅ የሚገኙ ሰነዶች ቅጂ

(b) ይህ መረጃ እና ሰነድ ከቀረበ በኋላ በአስር የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተጨማሪ መረጃ ወይም ይግባኝ የተጠየቀበትን ጉዳይ ውሳኔ የሚደግፉ ሰነዶችን ማቅረብ እና ግልባጭ ለይግባኝ ጠያቂው አካል መስጠት አለባቸው።

(c) በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከቀረበ በኋላ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ፣ ይግባኝ ጠያቂው አካል ከሱፐርኢንተንደንቱ ለቀረበው ምላሽ የሚሆን

r) በሌሎች የአሠራር ቅደምተከተል መመሪያዎች ላይ ያለው ውጤት

እነዚህ የአሰራር ሥርዓቶች ቀደም ሲል በቦርዱ የችሎት አጣሪ መርማሪ እና ቦርዱ ይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ወይም በቦርድ የሚካሄድ ችሎት፣ወይም በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በሥራ ላይ የዋሉትን ሌሎች ሥርዓቶች ሁሉ ይተካሉ።

## C. ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ይከለሳል።

ተዛማጅ ምንጮች፡- Md.Code Ann., Education Sections 4-205, 6-202, 6-203, and 7-305; Maryland Rules, Rule 1-203.

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** የፀደቀበት የውሳኔ ቁጥር 227-84፣ኤፕሪል 10, 1984፣ በውሳኔ ቁጥር 536-84፣ ኦክቶበር 9, 1984፣ እና በውሣኔ ቁጥር እንደገና ተስተካክሏል። በውሳኔ ቁጥር 333-86፣ ጁን 12, 1986፣ እና በውሳኔ ቁጥር 458-86፣ ኦገስት 12, 1986፣ ሥራ ላይ ውሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 550-88፣ ኦክቶበር 24, 1988፣ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 1050-91 ዲሴምበር 10, 1991፣ በውሳኔ ቁጥር 18-13፣ ጃኑወሪ 8፣ 2013 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁ. 315-14፣ ጁን 30/2014፤ ቴክኒካል ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ በውሳኔ ቁጥር 415-18፣ ሴፕቴምበር 11, 2018 ተሻሽሏል።